# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ አመሰራረት ........ 1

የኤጀንሲው ዓላማ ........ 2

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር ........ 2

የኤጀንሲው አደረጃጀትና የሰው ሃይል ........ 3

የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

ስዕላዊና ፅሑፋዊ የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description) ........ 5

ለሕብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ መስጠትን (ማደራጀት፣ አቅም መገንባት፣ ኢንስፔክት ማድረግና የሕግ ጉዳዮችን ማስፈፀም) በተመለከተ የስራ ሂደት መግለጫ (Process Description) ........ 5

የኦዲቱ ዓላማ ........ 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 7

የኦዲቱ አካባቢ ........ 8

የኦዲቱ  የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 8

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች ........ 9

ክፍል ሁለት ........ 10

የኦዲት ግኝቶች ........ 10

2.1 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ኅብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች/ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡ ድጋፎችን ተግባራዊ ለማድረግ የክትትል፣ የቁጥጥርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤ ........ 10

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን መከታተሉን በተመለከተ፣ ........ 10

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጠውን ድጋፍ በረጅምና በአጭር ጊዜ ዕቅድ ውስጥ ማካተቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 10

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ከመደራጀታቸው በፊት እንዲሁም ከተደራጁ በኂላ እንዲያድጉ ጥናትና ምርምር ማድረጉን እና የክልል ማስፋፊያ አካላት ጥናት እንዲያደርጉ እገዛ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 11

የህብረት ስራ ማህበራት በፌዴራል እና በክልል ስለመደራጀታቸው እንዲሁም የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ሊግ ማቋቋሙን በተመለከተ፣ ........ 13

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የስልጠና ተቋም ማቋቋሙን፣ ለሰጠው ስልጠና የስልጠና ፍላጎት ጥናት ማጥናቱን፣ ለህብረት ስራ ማህበራትና ለኅብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ስልጠና መስጠቱን እንዲሁም የክልል ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች ስልጠና ከመስጠታቸው በፊት የስልጠና ፍላጎት ጥናት እንደሚያጠኑ እና ስልጠናው ያመጣውን ውጤት የሚለካበት ስርዓት ስለመኖሩ፣ ........ 14

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ አሰጣጥ በተመለከተ የወጡ አዋጆችን እና ደንቦችን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች ማዘጋጀቱንና ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ማሰራጨቱን በተመለከተ፣........ 16

የሕብረት ስራ ማህበራት መመሪያዎች ሲዘጋጁ ሴቶችንና ወጣቶችን ሊያበረታታ በሚያስችል መልኩ መሆኑን እና ኤጀንሲው ለሕብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ አዘጋጅቶ በመላክ ክልሎች በጥቅም ላይ ማዋላቸውን መከታተሉን እንዲሁም ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ጋር በመሆን የህብረት ስራ ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት ስለመስራታቸው እና በዚህ ዙሪያ ስላጋጠሚቸው ችግሮች በየሩብ ዓመቱ መከታተሉን በተመለከተ፤..... 18

የህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኦዲት ስለመደረጉ፤.... 19

ኤጀንሲውና የሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የሚሰሩትን የኦዲት ሪፖርት ለሕብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አቅርበው በማስፀደቅ በኦዲት ሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነት ስለመከታተላቸው እና የማህበራትን የሂሳብ ምርመራ ውጤት መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ማህበር ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሰርተፊኬት መስጠታቸውን በተመለከተ። ........ 21

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁ ማህበራት የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣........ 22

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት በህብረት ስራ ጠቀሜታ፣ እንቅስቃሴና ዕድገት ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠራቸውን በተመለከተ፣ ........ 23

2.2 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በደንቡ መሠረት የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ መሆኑንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ 24

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ ማድረጉን እንዲሁም ህብረት ስራ ማህበራት የምርትና የገበያ ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ መደበኛ የሆኑ የመወያያ መድረኮች ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤........ 24

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና በየደረጃው የሚገኙ የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ተቀናጅተው የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት እንዲኖራቸው እና ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ እንዲሁም የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ እገዛ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤ ...................................... 25

የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ከማስፋፊያ አካላትና ከማህበራት ጋር ሪፖርቶችን፣ ጥናቶችን፣ ህትመቶችን፣ መመሪያዎችንና መረጃዎችን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደሚለዋወጥ እንዲሁም ከማስፋፊያ አካላት ጋር በሪፖርት አደራረግ፣ በስልጠና አሰጣጥና ስልጠናው ያመጣው ውጤት አለካክ ዘዴና ቁጥጥር ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of Understanding) መፈራረሙን እና መረጃዎችን በዳታ ቤዝ ስርዓት በማስደገፍ መያዙን በተመለከተ፣ ......................... 27

ክፍል ሦስት ........................................................................................................ 29

የመደምደሚያ ሃሳቦች ........................................................................................ 29

ክፍል አራት ........................................................................................................ 32

የማሻሻያ ሃሳቦች ................................................................................................ 32

አባሪ1 ................................................................................................................ *i-iii*

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ አመሰራረት**

1. የሕብረት ስራ ማህበር ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ነው፡፡

2. በሀገራችን የሕብረት ስራ ማህበራትን በዘመናዊ መልኩ ማደራጀት ከተጀመረ 50 ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሕብረት ስራ ማህበራትን ለማደራጀት አምስት የተለያዩ አዋጆች፣ አንድ የማሻሻያ አዋጅና አንድ ደንብ ከመውጣቱም በተጨማሪ አገሪቱ ከምትከተለው ፌዴራላዊ አወቃቀር አንጻር የሕብረት ስራ እንቅስቃሴን በአንድ ጥላ ስር ለመምራት በፌዴራል ደረጃ የማደራጀት፣ የመመዝገብ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ስልጠና፣ ምርምር እና ሌሎች የሙያና የቴክኒክ ድጋፎችን እንዲያገኙ የሚያስችል የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ እንዲሁም በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች እስከ ወረዳ ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ደረጃ የሕብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያና ማደራጃ ተቋማት እንዲቋቋሙ ተደርጓል ፡፡

3. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 274/1994 የሕብረት ስራ ኮሚሽን ግንቦት 6 ቀን 1994 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን በ1998 ዓ.ም የአስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ መጠሪያ ስሙ ኮሚሽን መሆኑ ቀርቶ የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ተብሎ እንዲጠራ ተወስኗል፡፡

4. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለሕብረት ስራ ማህበራት እድገት የሚበጁ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን በማጥናትና በማዘጋጀት እንደአስፈላጊነቱ ከክልሎች ጋር በመተጋገዝ ማህበራት ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡ በዚህም መሰረት የአነስተኛ የገጠር ፋይናንስ ተቋማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (Rural Financial Intermediation Programme) ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ለሰባት ዓመታት ፕሮግራም ተይዞለት እየተሰራ የነበረ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ሁለት ፕሮጀክቶች ማለትም የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት እና የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ፕሮግራም ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ዓመታት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡

5. የሕብረት ስራ ማህበራት በተለያየ የአደረጃጀት እርከን ተደራጅተዋል፡፡ የመጀመሪያው እርከን መሰረታዊ የሕብረት ስራ ማህበር የሚባል ሲሆን እስከ መጋቢት 30 2003 ዓ.ም በ20 የሕብረት ስራ ማህበራት ዓይነቶች 38,454 ማህበራትን ያቀፈና ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች የተቋቋመ ነው፡፡ ሁለተኛው የሕብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀት እርከን የሕብረት ስራ ሕብረት /ዩኒዩን/ ሲሆን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተመሳሳይ አላማ እና ተግባር ያላቸው መሰረታዊ የሕብረት ስራ ማህበራት የሚያቋቁሙት የሕብረት ስራ ማህበር ነው፡፡ ይህም እርከን በ15 ዓይነት የሕብረት ስራ ማህበራት 245 ዩኒየኖችን ያቀፈ ነው፡፡ ሶስተኛው እርከን ፌዴሬሽን በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ባላቸው ዩኒየኖች ይመሰረታል፡፡ በዚህም እርከን አራት የሕብረት ስራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች በአባላት ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ ተመስርተዋል፡፡ አራተኛው እርከን ሊግ ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመሰረት ነው፡፡

## የኤጀንሲው ዓላማ

6. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ዋና አላማ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 274/1994 መሠረት በገጠርና በከተማ የሚኖረው ሕዝብ በአካባቢው ሃብት ላይ በመመስረት የተለያዩ ዓይነትና ደረጃ ባላቸው የሕብረት ስራ ማህበራት እየተደራጀ የሚገጥመውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች በጋራ እንዲፈታና በራሱም ላይ እንዲተማመን ማድረግ ነው፡፡

## የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

7. ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

- ለሕብረት ስራ ማህበራት እንቅስቃሴና ዕድገት የሚበጁ የፖሊሲ ሃሳቦችንና የሕግ ረቂቆችን አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣
- የሕብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀት በሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 መሠረትና በዓለም አቀፍ የሕብረት ሥራ መርሆዎች መሠረት እንዲደራጁ ያበረታታል፣
- በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋመውን የሕብረት ሥራ ማሠልጠኛ ተቋም ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

- የሕብረት ስራ ዕሴቶች፣ መርሆዎች፣ አደረጃጀት እና ጠቀሜታ በሕብረተሰቡና በትምህርት ተቋማት ይበልጥ እንዲታወቁ ያደርጋል፣

- በፌዴራል ደረጃ የሚደራጁ የሕብረት ስራ ማህበራትን ሂሳብ ይመረምራል፣ ሂሳብ አጣሪም ይመድባል፣ ሲፈርሱም ከመዝገብ ይሰርዛል፣ በመላ ሀገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ የሕብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣

- የሕብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት ወይም ዋጋ እንዲኖራቸው፣ ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ እና የእጅ ጥበብ ምርቶች እንዲያድጉ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣

- ለሕብረት ሥራ ዕድገት የሚበጁ ፕሮጀክቶችን በማጥናትና በማዘጋጀት እንደአስፈላጊነቱ ከክልሎች ጋር በመተጋገዝ ማህበራት ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፣

- በክልል ለሚደራጁ ቢሮዎችና የሕብረት ሥራ ማህበራት የቴክኒክና የሙያ እገዛ ያደርጋል፣

- እንደየሕብረት ሥራ ማህበራቱ ዓይነትና ደረጃ ሊለዋወጥ የሚችል የማህበራት ሞዴል የመተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣

## የኤጀንሲው አደረጃጀትና የሰው ሃይል

<u>የኤጀንሲው አደረጃጀት</u>

8. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለንግድ ሚኒስቴር ሲሆን በአንድ ዋና ዳይሬክተርና በአንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ይመራል፡፡ ተጠሪነታቸው ለዋናው ዳይሬክተር የሆኑ የኦዲት መምሪያ፣ የሰው ሃብትና ንብረት ስራ አመራር መምሪያ፣ የፋይናንስ መምሪያ፣ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል፣ የፕላንና ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ አገልግሎት፣ የገጠር ፋይናንስ ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስተባበሪያና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ያሉት ሲሆን የሕብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ቁጥጥር ዳይሬክሲዮን ተጠሪነቱ ለምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ነው፡፡

<u>የሰው ኃይል</u>

9. ኤጀንሲው በሰኔ ወር 2003 ዓ.ም መጨረሻ 67 ቋሚ ሠራተኞች የነበሩት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 28 (41.8%) ሴቶች፣ 39(58.2%) ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል

በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 18 (27.3%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 11(16.4%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ/10+3/ 22 (32.8%)፣ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ11 (16.4%) እንዲሁም ከሁለተኛ ደረጃ በታች ያሉ 5 (7.5%) ሰራተኞች አሉት፡፡

**የፋይናንስ ምንጭ**

10. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ስራውን የሚያንቀሳቅሰው ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በ2001፣ በ2002 እና በ2003 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 7,625,200፣ 8,808,148 እና 9,300,217 መደበኛ በጀት በድምሩ ብር 25,733,565 ያህል ከመንግስት ፀድቆ ለሚተገብራቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የተመደበለት ሲሆን ከተመደበለት በጀት ውስጥ በ2001 ዓ.ም ብር 7,044,642.26፣ በ2002 ብር 8,238,886.17 እና በ2003 ብር 9,133,806.93 በድምሩ ብር 24,417,335.36 ጥቅም ላይ አውሏል፡፡

## ስዕላዊና ፅሑፋዊ የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

**<u>ለሕብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ መስጠትን (ማደራጀት፣ አቅም መገንባት፣ ኢንስፔክት ማድረግና የሕግ ጉዳዮችን ማስፈፀም) በተመለከተ የስራ ሂደት መግለጫ (Process Description)</u>**

**የፌዴራል የሕብረት ስራ ማህበራትን ማደራጀት፣በ ፌዴራል እና በክልሎች የሕብረት ስራ ማህበራት አቅም መገንባት፣ ኢንስፔክት ማድረግና እና የሕግ ጉዳዮችን ማስፈፀም**

ማደራጀት →
- ማደራጀት ጥያቄ
- የአደረጃጀት መመሪያ
- ጥናት ማካሄድ
- ለምዝገባ ማቅረብ

መመዝገብ →
- የምዝገባ ጥያቄ
- ሰነዶችን መመርመር
- መመዝገብ

ኢንስፔክት ማድረግ →
- እስትራቴጂክ ዕቅድ
- የኢንስፔክሽን ስራ ማከናወን
- ውጤቱን ተግባራዊ ማድረግና መከታተል

መሠረዝ →
- የፍ/ቤት ትዕዛዝ፣ የአባላት ጥያቄ ወይም ኪሳራ
- ጥያቄውን ማጣራት
- የሕ/ስ/ማህበራቱ በመፍረስ ላይ መሆናቸውን ማሳወቅ፣ንብረታቸውን መረከብ እና ማስረጃዎችን ማሰባሰብ
- ሂሳባቸውን አጣርቶ ለባለድርሻ ማከፋፈልና ሪፖርት ማቅረብ
- ከመዝገብ መሰረዝና ማሳወቅ

ስልጠና መስጠት →
- የማህበራትና የማህበራት ማስፋፊያ አካላት የስልጠና ፍላጎት ጥያቄ
- የፍላጎት ጥናት ማካሄድና የስርዐተ ትምህርት ማዘጋጀት/ማሻሻል
- ማንዋል ማዘጋጀት/ማሻሻል
- አሰልጣኞችን መርጦ ስልጠና ማካሄድ
- ስልጠናው ያመጣውን ለውጥ መገምገም
-

የስራ መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር፣ ጥናት ማካሄድ እና መረጃ ማሰባሰብ →
- የስራ መመሪያዎችን መለየት/ማሻሻል
- ማስተዋወቅና ተግባራዊ ማድረግ

ህጋዊ ሰውነት ያላቸው በእውቀት የተገነቡ እና ህግና ደንብን የተከተሉ የሕ/ስ/ማህበራትን ማፍራት

## *ፅሁፋዊ የሥራ ሂደት መግለጫ* (Process Description)

11. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የኤጀንሲው እና የክልል ህብረት ስራ ማህበራት አባላት የሚመሩበትን የስራ መመሪያ ያዘጋጃል፣ መመሪያውንም ያሻሽላል፤ እንዲሁም መመሪያዎቹ በተሟላ እና ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ እንዲተገበሩ የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፡፡

12. የህብረት ስራ ማህበራትን ለማስፋፋት ኤጀንሲው እና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት አባላት ለመደራጀት የሚያቀርቡትን ጥያቄ ተቀብለው የአዋጪነት ጥናት በማካሄድ ለምዝገባ ማቅረብ፣ ለመደራጀት የቀረቡትን የአባላት ሰነድ መርምሮ መመዝገብ፣ በስትራቴጅክ ዕቅድ መሰረት የተደራጁ ማህበራትን ኢንስፔክት ማድረግ፣ ውጤቱን መሰረት አድርጎ መከታተል፣ በማህበራት የስልጠና ፍላጎት ጥያቄ መሰረት የፍላጎት ጥናት ማካሄድ፣ የስርዓተ ትምህርት እና የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ በየጊዜው የሚከሰቱ ለውጦችን መሰረት በማድረግ ለስርዓተ-ትምህርቱ እና ለስልጠና ማንዋሎች ማሻሻያ ማድረግ፣ በየክልሉ ከሚገኙ የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት አሰልጣኞችን መርጦ ለተመረጡ አሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣ የተሰጡ ስልጠናዎች በማህበራት እና በማስፋፊያ አካላት ላይ ያመጣውን ለውጥ መገምገም፣ ለህብረት ስራ ማህበራት የሕግ ጉዳዮችን በመከታተል እና በማስፈፀም እገዛ በማድረግ ሕጋዊ ሰርተፊኬት ያላቸውን እና ሕግና ደንብን የተከተሉ የህብረት ስራ ማህበራትን የማፍራት እና የማስፋፋት የጋራ ኃላፊነት ለኤጀንሲው እና ለክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ተሰጥቷል፡፡

13. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከላይ ከተገለጹት ተግባራት በተጨማሪ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላትን የማበረታታት እና የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

14. የኦዲቱ ዓላማ ለሕብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና አፈፃፀሙ ተግባራዊ መሆኑን ለመገምገም ይህንን ስራ ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ሃላፊነቱን በአግባቡ መወጣቱን እና የዓለም አቀፍ መርሆችን የተከተለ የሕብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀት

መፍጠሩን ለማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ**

15. ኦዲቱ የሸፈነው ሦስት የበጀት ዓመታት ማለትም ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ለሕብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋውን የአሰራር ስርዐት አፈፃፀምና ውጤታማነት በተመለከተ የተሠሩትን ሥራዎች ነው፡፡ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ሲሆን፣ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት፣ በፌዴራል እና በክልል ያሉትን መሰረታዊ ሕብረት ስራ ማህበራት፣ ዩኒየኖችና ፌደሬሽኖችን በናሙና መርጦ በማየት፣ የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ፣ ለሚመለከታቸው የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ፣ የክልል ማስፋፊያ አካላት እንዲሁም ለሌሎች ባለድርሻ አካላትና ለህብረት ስራ ማህበራት የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና መጠይቆችን በመላክ ነው፡፡

16. በዚህም መሠረት ለማህበራት ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ዘጠኝ የክልልና ሁለት የመስተዳድር ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ውስጥ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለሕብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ ለአንድ ወረዳና አንድ ዞን ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች፣ ለሁለት መሰረታዊና ሁለት ዩኒየን፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሶቦች ሕዝቦች ክልል የህብረት ስራ ማስፋፊያና ግብይት ቢሮ፣ አንድ ወረዳ፣ ሶስት መሰረታዊ፣ አንድ ዩኒየንና አንድ ፌዴሬሽን፤ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለሕብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ አንድ የወረዳ ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት፣ አንድ መሰረታዊና ሁለት ዩኒየን ፤ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ፣ ሁለት የዞንና ሁለት የወረዳ ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች፣ ስምንት መሰረታዊ፣ ሶስት ዩኒየንና ሁለት ፌዴሬሽን፤ በአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ማስፋፊያ ቢሮ ለሕብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ልማት ዋና የሥራ ሂደት፣ ሦስት የክፍለ ከተማ የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያና ልማት ዋና የስራ ሂደቶች፣ ሶስት የወረዳ ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች፣ ሁለት መሰረታዊና ሁለት ዩኒየን እና ለፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና በስሩ ላለው አንድ መሰረታዊ ሕብረት ስራ ማህበር በድምሩ ለአስራ ስባት መሰረታዊ ሕብረት ስራ ማህበራት፣ ለአስር ዩኒየኖች፣ ለሶስት ፌዴሬሽኖች፣ ለሶስት ክፍለ

ከተሞች፣ ለስምንት የወረዳና ለሶስት የዞን ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች እና ለአምስት ማስፋፊያ አካላት፣ በአካል በመገኘት መረጃዎችን በመከለስና ለሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

17. እንዲሁም በናሙና ለተመረጡ 32 መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትና ለአራት ባለድርሻ አካላት (የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ፣ የአዲስ አበባ መስተዳድር መሬት አስተዳደር ቢሮ) መጠይቆችን (Survey Questionnaire) በመላክ ከሰባት መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በተጨማሪም ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴርና ለንግድ ሚኒስቴር በአካል በመገኘት መረጃዎችን በመከለስና ለሃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ

18. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት በአግባቡ መፈፀሙንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

19. ከላይ በተገለፀው የኦዲት አካባቢ ሁለት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በመጀመሪያው የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሶስት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

እነርሱም፦

1. ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የወጡ የኤጀንሲው አዋጆች እና የሕብረት ስራ ማህበራት ደንቦችን ተፈጻሚ እና ውጤታማ ለማድረግ ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርአት እንዲሁም የክትትል ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

    1.1 ማህበራት ሲደራጁ በጥናት ላይ ተመስርተው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሚሰራ እና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ የሚደረጉ መሆኑን ማረጋገጥ፡

1.2 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለፌዴራል እና ለክልል ህብረት ስራ ማህበራት የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የአቅም ግንባታ እና የፋይናንስ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፤

1.3 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ቀልጣፋ የሆነ የህብረት ስራ ማህበራት ክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤

2. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በደንቡ መሠረት የተሰጠውን ሀላፊነት በብቃት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የዘረጋ መሆኑንና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ፡፡

## የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች

20. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡ ሁለት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ሶስት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 43 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ለሕብረት ስራ ማህበራት የወጡ አዋጅ እና ደንቦች፣ በኤጀንሲው የሚገኙ የተለያዩ የአፈፃፀም መመሪያዎች፣ መፃፃፎች (correspondence letters) እና ቃለ-መጠይቆች ናቸው"" መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ተያይዘዋል""

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**2.1 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ኀብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች/ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡ ድጋፎችን ተግባራዊ ለማድረግ የክትትል፣ የቁጥጥርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት መዘርጋታቸውን በተመለከተ፤**

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን መከታተሉን በተመለከተ፣**

21. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ 2003 ዓ.ም የህብረት ስራ ፖሊሲን ለማስፀደቅ በዕቅድ ከመያዝ ባለፈ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ እንዲቀረፅ አላደረገም፡፡

23. ስለጉዳዩ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ኃላፊዎች በዚህ ዙሪያ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ የህብረት ስራ ፖሊሲም እንደሆነ ገልፀዋል ፡፡

24. ይሁን እንጅ በኦዲቱ ወቅት ፖሊሲ ባለመኖሩ ምክንያት የህብረት ስራ ማህበራት አቅጣጫና ዕድገት አመላካች እንዳይኖር ማድረጉ፣ የህብረት ስራ ማህበራትን ዕድገት ለመለካት አስቸጋሪ መሆኑ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን መስተጋብር ለይቶ ማወቅ አለመቻሉ፣ ሕብረተሰቡ ስለ ህብረት ስራ ማህበራት በቂ ግንዛቤ እንዳይኖረው ማድረጉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጠውን ድጋፍ በረጅምና በአጭር ጊዜ ዕቅድ ውስጥ ማካተቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

25. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በሚያዘጋጀው የስትራቴጅክ ዕቅድ ውስጥ ለህብረት ስራ ማህበራት በሚሰጠው ድጋፍ ዙሪያ የሚሰራውን ሥራ ሊያካትትና ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል፣ በስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት ዓመታዊ እቅድ ሊያዘጋጅ፣ እቅዱን ተግባራዊ

በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ እና በየጊዜው በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት መሰረት በሚታዩ ክፍተቶች ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

26. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2000-2002 ዓ.ም እና ከ2003-2007 ዓ.ም ባዘጋጃቸው ስትራቴጂክ ዕቅዶች ውስጥ 2204 መጋዘኖች ተገንብተው ለህብረት ስራ ማህበራት ለመስጠት፣ 3 የህብረት ስራ ባንኮችንና 2 ኢንሹራንሶችን ለማቋቋም፣ የግብይት መረጃ ልውውጥ ስርዐትና ትስስር ለመዘርጋት እንዲሁም የስልጠና ፍላጎት ጥናት በ2001 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም ለማጥናት ዕቅድ ቢይዝም ተግባራዊ አለማድረጉ ተረጋግጧል፡፡

27. ከ2001-2003 ዓ.ም ባሉት የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ላይ በአለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) በየጊዜው የሚወጡ ውሳኔዎችንና ስምምነቶችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተግባራዊ ለማድረግ፣ የህብረት ስራ ማህበራትን እንቅስቃሴ ሊያግዙ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ለማዘጋጀት እና በፌዴራል ደረጃ ህብረት ስራ ማህበራትን ለማደራጀት (በመሰረታዊ፣ በዩኒየን እና በፌደሬሽን) በየአመቱ እቅድ ቢይዝም አለማከናወኑ፤

28. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የህብረት ስራ ኢንሹራንስ ፣ ባንክ ማቋቋም እና መጋዘኖች መገንባትን በተመለከተ በስትራቴጅክ ዕቅድ የሴክተሩን በማካተት ቢያቅዱም ሆኖም ግን ኤጀንሲው በዚህ ረገድ እንቅስቃሴ እንዳላደረገ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በአለም አቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) የሚወጡ ውሳኔዎችንና ስምምነቶችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተግባራዊ የማድረግ ስራ ውሳኔዎቹና ስምምነቶቹ ባለመኖራቸው ምክንያት ተግባራዊ አለመደረጋቸውን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ስምምነቶቹ መኖራቸው እና ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተረጋግጧል፡፡

## የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ከመደራጀታቸው በፊት እንዲሁም ከተደራጁ በኂላ እንዲያደጉ ጥናትና ምርምር ማድረጉን እና የክልል ማስፋፊያ አካላት ጥናት እንዲያደርጉ እገዛ ማድረጉን በተመለከተ፣

29. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የአዋጭነት እና የሶሽዮ ኢኮኖሚ ጥናት እንዲያጠኑ እገዛ ሊያደርግ፣ እንዲሁም ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት (እድር፣መረዳጃ ማህበር ወዘተ) ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናት እና ምርምር ሊያደርግ ይገባል፡፡

30. ክልሎች ህብረት ስራ ማህበራትን በብዛት የሚያደራጁ ቢሆንም አደራጅ ባለሙያዎችን የአዋጭነት ጥናት እንዲያጠኑ በ2001 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም በተግባር በማሳየት እገዛ ያላደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ በታዩት የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የቤኒሻንጉልና የደቡብ ክልል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች የሶሽዩ ኢኮኖሚ ጥናት እንዲያጠኑ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እገዛ ያላደረገላቸው ሲሆን በክልል ወረዳዎችና ዞኖች የሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት አደራጁ በራሱ በመሰለው አስተያየት የሚደራጁ እንጂ ለጥናት ተብሎ የተዘጋጀ መመሪያ አለመኖር፤ በክልሎች የሚሰራው የአዋጭነት ጥናት ወጥነት የሌለው መሆኑ (በቅጽ፣ ከሌላ ጥናት ጋር አንድ ላይ በማድረግ፣ የንግድ ዕቅድን እንደ አዋጭነት በመውሰድ መሰራቱ)፤ እንዲሁም ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት (እድር፣ መረዳጃ ማህበር ወዘተ) ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናት እና ምርምር አለማድረጉ ታውቋል፡፡

31. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሶሽዮ ኢኮኖሚም ሆነ የአዋጭነት ጥናት እንደሚከናወን ቢገልጹም ማስረጃውን ግን ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ የአዋጭነት ጥናትን በተመለከተ ለክልሎች ስልጠና በመስጠት አቅጣጫ ቢያሳይም የክትትል ማነስ መኖሩንና ተግባራዊ መደረግ ላይ ችግር መኖሩን፣ የሶሽዩ ኢኮኖሚ ጥናት ግን እንዲጠና በክልሎች ያልተጠየቀና መመሪያ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱና የጠየቀ ተገልጋይም ባለመኖሩ ምክንያት አለመዘጋጀቱን በነባራዊ ሁኔታው ላይ የጠቀሱ ቢሆንም በመውጫ ውይይት ወቅት ግን የአደረጃጀት መመሪያ ውስጥ የሶሽዮ ኢኮኖሚ እና የአዋጭነት ጥናት ተካቷል በሚል የተቃረነ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ማህበራትን ከባህላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበር ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበርነት የሚያድጉበትን ጥናትና ምርምር ከተግባርና ሃላፊነት አኳያ በአዋጁ ላይ ያለ ቢሆንም አለመስራቱን ለዚህም እንደ አስረጂነት ዕቁብና እድር ካላቸው ጥንካሬ አንፃር የኤጀንሲው የትኩረት አቅጣጫ አለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

32. ይህም በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበራት ቀጣይነት ባለው መልኩ ትርፋማ እንዳይሆኑ፣ ለኪሳራ እንዲጋለጡ ህልውናቸው ላይ ስጋት እንዲፈጠርባቸው ማድረጉን እንዲሁም ኤጀንሲው በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ ህብረት ስራ ማህበርነት ተለውጠው ውጤታማ እንዳይሆኑ እንቅፋት መፍጠሩ ታውቋል፡፡

**የህብረት ስራ ማህበራት በፌዴራል እና በክልል ስለመደራጀታቸው እንዲሁም የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ሊግ ማቋቋሙን በተመለከተ፣**

33. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ሥራ ማህበራትን በፌዴራልና በክልል ደረጃ ሊያደራጅ እና እንዲደራጁ እገዛ ሊያደርግ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ የሕብረት ሥራ ሊግ ሊያቋቁም ይገባል፡፡

34. በኤጀንሲውና በክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት እስከ 2003 ዓ.ም 38,703 ህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተዋል፡፡ ኤጀንሲው ግን በፌዴራል ደረጃ ያቋቋመው አንድ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር ብቻ ሲሆን ዩኒየንና ፌዴሬሽን አላቋቋመም፡፡ ይህን በተመለከተ ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር ስምምነት ላይ ባለመደረሱ ምክንያት በፌዴራል ደረጃ የህብረት ስራ ፌዴሬሽን እንዳልተቋቋመ የገለፀ ሲሆን በክልል ደረጃ በኦሮሚያ ሁለት ፌዴሬሽን፣ በትግራይና በደቡብ ክልሎች አንድ አንድ ኅብረት ሥራ ፌዴሬሽን መቋቋሙ ታውቋል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት የታዩት የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ/ቢሮ/ጽ/ቤት (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ አዲስ አበባ፣ ቤንሻንጉል) ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ በፌዴራል ደረጃ ፌደሬሽን ባለመቋቋሙ ምክንያት አገሪቱ ከዓለም አቀፍ የህብረት ስራ ህብረት (International Cooperative Alliance) ማግኘት የሚገባትን የአባልነት ጥቅሞችና የልምድ ልውውጥ እንዳታገኝ ማነቆ እንደሆነ፣ በክልል ደረጃ የተደራጁት ፌደሬሽኖች በቅንጅት እንዳይሰሩና ሀገራዊ ትስስር እንዳይፈጥሩ እንዳደረገ፣ ህብረት ስራ ማህበራት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ድጋፍ ማግኘት እንዳይችሉና ከምርት ግብይት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ፣ እንዲሁም ከጅምላ አከፋፋዮች ጋር ቀጥተኛ ትስስር መፍጠር እንዳላስቻለ የገለፁ ሲሆን ከዚህም ሌላ የህብረት ሥራ ሊግ ለማቋቋም በአገር አቀፍ ደረጃ ሁለትና ከዚያ በላይ ፌዴሬሽኖች መቋቋም ያለባቸው በመሆኑና ይህም ባለመከናወኑ የህብረት ስራ ሊግ አለመቋቋሙ ታውቋል፡፡

36. እስከ ግንቦት 2003 ዓ.ም ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች (ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌና አፋር) ከተደራጁት 1539 ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ

ከ2001-2002 ዓ.ም 3 ህብረት ስራ ማህበራትን ብቻ ያደራጀ ሲሆን በ2003 ስለማደራጀቱ መረጃ አልተገኘም፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የስልጠና ተቋም ማቋቋሙን፣ ለሰጠው ስልጠና የስልጠና ፍላጎት ጥናት ማጥናቱን፣ ለህብረት ስራ ማህበራትና ለኅብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ስልጠና መስጠቱን እንዲሁም የክልል ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች ስልጠና ከመስጠታቸው በፊት የስልጠና ፍላጎት ጥናት እንደሚያጠኑ እና ስልጠናው ያመጣውን ውጤት የሚለካበት ስርዓት ስለመኖሩ፣**

37. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ የህብረት ስራ ማሰልጠኛ ተቋም በማቋቋም በፌዴራል ለሚሰጡ ስልጠናዎች የስልጠና ፍላጎት ጥናት በማጥናት እንዲሁም የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለሚሰጡት ስልጠና የስልጠና ፍላጎት ጥናት እንዲያደርጉ በመከታተል ለሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት አመራሮች፣ ባለሙያዎችና ለህብረት ስራ ማህበራት በሂሳብ አያያዝ፣ በሕግ ጉዳዮች ወዘተ ዙሪያ ስልጠና ሊሰጥና የተሰጠው ስልጠና ያመጣውን/ያስገኘውን ውጤት የሚለካበት ስርአት ሊኖር ይገባል፡፡

38. የፌዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ የህብረት ስራ ማሰልጠኛ ተቋም ባለማቋቋሙ የሚሰጡ ስልጠናዎች የስልጠና ፍላጎትን መሠረት ያላደረጉና ያለውን የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ታስቦ የሚሰጡ አለመሆን፤ አብዛኛውን ጊዜ ስልጠና የሚሰጠው አለታዊ ችግሮችን ለመፍታት እንጂ የተቀናጀ እና ጥናትን መሠረት ያደረገ ችግርን በዘላቂነት እንዲፈታ ታስቦ የሚሰጥ ስልጠና አለመኖር፤ በፌዴራል ደረጃ እና በክልል የሚሠጡ ስልጠናዎችን ተመጋጋቢ አለማድረግ እና ድግግሞሽን (ተመሣሣይ ስልጠና ለተመሣሣይ ሰልጣኞች መስጠትን) አለማስቀረት እንዲሁም ስልጠናው ያመጣውን ውጤት መለካት እንዳልተቻለ ተረጋግጧል፡፡

39. የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በ2002 ዓ.ም አንድ ጊዜ የስልጠና ፍላጎት ጥናት ቢያጠናም በኦዲት ወቅት ከታዩት 8 የወረዳ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች መካከል ከ2001-2003 ዓ.ም ስልጠና ያገኙት 3 የወረዳ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች ሲሆኑ ስልጠና ከማግኘታቸው በፊት የስልጠና ፍላጐታቸውን አልተጠየቁም፡፡ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ህብረት ስራ ማህበራት በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ከ2001-2003 ዓ.ም ሶስቱ ስልጠና ሲሰጣቸው የስልጠና ፍላጐት ያልተጠየቁ ሲሆን 1 ህብረት ስራ ማህበር ደግሞ የስልጠና ፍላጎት ቢጠየቅም የተሰጠው ስልጠና ግን በተጠየቀበት መሠረት ሳይሆን በኤጀንሲው ኘሮግራም መሠረት መሆኑ ታውቋል፡፡

40. በሰርቬይ እና በአካል ከታዩ 37 ሕብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 20 (54.05%) የሚሆኑት ከ2001-2003 ዓ.ም ከፌዴራሉም ሆነ ከክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ስልጠና አላገኙም፡፡ እንዲሁም በኦዲት ወቅት ከታዩት 8 የወረዳ ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች ውስጥ 4ቱ ከ2001-2003 ዓ.ም ከፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ስልጠና ያላገኙ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል የታዩ 2 የወረዳ ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ከ2001-2003 ዓ.ም ከአንድ ጊዜ በስተቀር በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ስልጠና አላገኙም፡፡ ከወረዳዎች በተገኘው ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት በጊምቢና በጎማ ወረዳ ከተደራጁ 112 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 96ቱ (86%) ከ2001- 2003 ዓ.ም ስልጠና አላገኙም፡፡

41. ከዚህ በተጨማሪም በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የሚሰጡ ስልጠናዎች ንድፈ ሃሣብ /theory/ ላይ ብቻ በመመስረታቸውና ከተግባር ሥራ ጋር የተቆራኙ ባለመሆናቸው፣ የሰልጣኙን ፍላጎት ማሟላት አልቻሉም፡፡

42. ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት በስራቸው ላሉት የኅብረት ሥራ ባለሙያዎች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ስልጠና ሲሰጡ ፍላጐትን መሠረት ያደረገ መሆኑን ወይም የስልጠና ፍላጐት ጥናት እንደሚያጠኑ የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ አልተከታተለም፡፡ በዚህ ዙሪያ ለፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በቀረበ መጠይቅ በባለሙያ እጥረትና የስልጠና ተቋም ባለመኖሩ ምክንያት ክልሎች ለሰጡት ስልጠና የስልጠና ፍላጎት ጥናት እንደሚያጠኑ አለመከታተሉን፣ የህብረት ስራ ማሰልጠኛ ተቋም ለማቋቋም በጀት እንደሌለው እንዲሁም እስከ 2003 አጋማሽ ስልጠናዎች በውጭ ባለሙያ ይሠጡ ስለነበር አብዛኛውን ጊዜ ንድፈ ሃሣብ ላይ ያተኩሩ እንደነበርና ከዚያ ወዲህ ግን በራሱ ባለሙያዎች በተግባር የተደገፈ ስልጠና መስጠት መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

43. የፌዴራል ኅብረት ሥራ አጀንሲ ለኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ባለሙያዎችና ለኅብረት ሥራ ማህበራት ለሠጠው ስልጠና ያመጣውን/ያስከተለውን/ ውጤት አልለካም፤ የስልጠና ውጤት የሚለካበት ስርዓትም በኤጀንሲው አልተዘረጋም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የሚሠጡ ስልጠናዎችን ለማቀድ እና በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ያስከተለውን ውጤት ለማወቅ እና ለመገምገም አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው ለክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት የአሠልጣኞች ስልጠና ቢሰጥም አሠልጣኞች በሄዱበት ቦታ ስልጠናውን ተግባራዊ ማድረጋቸውን አልተከታተለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 4

ክልሎች መካከል በ4ቱም የክልል ኀብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት የተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት አልተለካም፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ አሰጣጥ በተመለከተ የወጡ አዋጆችን እና ደንቦችን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች ማዘጋጀቱንና ለህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ማሰራጨቱን በተመለከተ፣**

44. ኤጀንሲው ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ አሰጣጥን በተመለከተ የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

45. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጆችና ደንቦች ተግባራዊ ለማድረግ ካዘጋጃቸው 20 የአፈፃፀም መመሪያዎች ውስጥ ለክልሎች አስሩን መመሪያዎች የላከ ቢሆንም የተቀሩትን አስር መመሪያዎች የላከበትን ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑና ከተላኩትም ውስጥ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ 5 መመሪያዎች አለመገኘታቸው እንዲሁም የክልል ማስፋፊያ አካላት እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ መመሪያዎችን በማሻሻል ለዞኖች እና ለወረዳዎች እንደማይልኩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

46. በ2003 ዓ.ም በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ክልሎችና መስተዳድሮች በስራ መመሪያ ዝግጅትና አተገባበር ዙሪያ በኤጀንሲው በተጠናው ጥናት በአማካይ 78% መመሪያ አተገባበራቸው ደካማ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

47. በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና በክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በእርጅና፣ በጡረታና በህመም ምክንያት ከአባሎቻቸው ጋር እኩል መሳተፍ ያልቻሉ አባላትን በተመለከተ ግልፅ የሆነ መመሪያ አለመዘጋጀቱ፡፡ እንዲሁም ህብረት ስራ ማህበራት ማግኘት ስላለባቸው ቦታ ግልፅ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ ምክንያት በኦዲቱ ወቅት ከታዩት በአማራ 2፣ በኦሮሚያ 9፣ በደቡብ 2፣ በአዲስ አበባ 2 እና በቤንሻንጉል 1 ህብረት ስራ ማህበራት ለጠየቁት የቦታ ጥያቄ ከ1ወር እስከ 6ወር መልስ ሳያገኙ መቅረታቸው፣ በኦሮሚያ ክልል የንጋት ኮከብ የእጅ ባለሙያ ህብረት ስራ ማህበር ቦታ በሊዝ እንዲገዛ መደረጉ እና 3 ማህበራት (የበዳዲና ረቢ የማዕድን አምራቾች ህብረት ስራ ዩኒየን፣ መልካ አዋሽ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየንና የጊቤ ዴዴሳ የገበሬዎች ሁለገብ ህብረት ስራ ዩኒየን) ለመስሪያ ቦታና ለመጋዘን ኪራይ ብር 232,100 በማውጣት ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸው ታውቋል፡፡ በአጠቃላይ

በአማራ ክልል 475 እንዲሁም በኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል፣ በአዲስ አበባና በደቡብ ክልሎች 6 ህብረት ስራ ማህበራት የቦታ ችግር እንዳለባቸውና መፍትሔ ማግኘት እንዳልቻሉ በኦዲቱ በተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

48. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ስለሚያወጡት ፈቃድ እና የሚከፍሉትን ቀረጥ በተመለከተ የአፈፃፀም መመሪያ አላዘጋጀም፡፡

49. በዚህ ዙሪያ የክልል ማሥፋፊያ አካላት ኃላፊዎች ህብረት ስራ ማህበራት ለሚያነሱት ጥያቄ በቂ መልስ ለመስጠት መቸገራቸውን እና የህብረት ስራ ማህበራትን አዋጅ በግልፅ የሚያስረዳ የአፈፃፀም መመሪያ በሚመለከተው አካል ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት በህብረት ስራ ማህበራት አሰራር ላይ ችግር መፍጠሩን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የንግድ ሚኒስቴር የንግድና ምዝገባ ክፍል የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የህብረት ስራ አዋጅ ቁጥር 147/91 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/96 ላይ ማህበራት ከገቢ ግብር ነፃ የሚሆኑበት፣የኢንቨስትመንትና የንግድ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው ከህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በወሰዱት ሰርተፊኬት መስራት የሚችሉበት እና ለማንኛውም ኢንቨስተር የተፈቀደው ማበረታቻ ለህብረት ስራ ማህበራትም የሚፈቀድበት ሁኔታዎችን በተመለከተ አዋጁ የቆየ መሆኑን፣ እንዲሁም ያለ ንግድ ፈቃድ መስራትን በተመለከተ በ2002 ዓ.ም ለአገሪቱ የወጣው አዋጅ ቁጥር 686/2002 እንደሚሽረው እና ይህም ማንኛውም በንግድ ላይ የተሰማራ አካል የንግድ ፈቃድ ማውጣት እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለማህበራት ግንዛቤ ማስጨበጥ ወይም አዋጁ እንዲሻሻል ጥረት ማድረግ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

50. ይህም በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበራት የቦታ ጥያቄ ምላሽ እንዳያገኝ፣ ስለሚያወጡት ፈቃድ እና የሚከፍሉትን ቀረጥ እንዲሁም ህብረት ስራ ማህበራትን በተመለከተ የሚወጡ አዋጆች ላይ ግንዛቤ እንዳይጨብጡና በእድሜና በህመም ምክንያት ከማህበር የሚወጡ አባሎች መብታቸውን በግልፅ እንዳያውቁ አድርጓል፡፡

**የሕብረት ስራ ማህበራት መመሪያዎች ሲዘጋጁ ሴቶችንና ወጣቶችን ሊያበረታታ በሚያስችል መልኩ መሆኑን እና ኤጀንሲው ለሕብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ አዘጋጅቶ በመላክ ክልሎች በጥቅም ላይ ማዋላቸውን መከታተሉን እንዲሁም ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ጋር በመሆን የህብረት ስራ ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት ስለመስራታቸው እና በዚህ ዙሪያ ስላጋጠሟቸው ችግሮች በየሩብ ዓመቱ መከታተሉን በተመለከተ፤**

51. የሕብረት ስራ ማህበራት መመሪያዎች ሲዘጋጁ ሴቶችንና ወጣቶችን ሊያበረታታ በሚያስችል መልኩ ሊሆን እና ኤጀንሲው ለሕብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ አዘጋጅቶ በመላክ ክልሎች በጥቅም ላይ ማዋላቸውን ሊከታተል እንዲሁም ኤጀንሲውና የክልል ሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለሕብረት ስራ ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት ማህበራት ስለመስራታቸውና በዚህ ዙሪያ ስላጋጠሟቸው ችግሮች በየሩብ ዓመቱ ሊከታተሉ ይገባል፡፡

52. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2000-2002 ዓ.ም እና ከ2003-2007 ዓ.ም ባዘጋጃቸው ስትራቴጂክ ዕቅዶች በኅብረት ሥራ ማህበራት የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳትፎ/ቁጥር/ እንደሚጨምር ቢያስቀምጥም ያዘጋጃቸው መመሪያዎች ውስጥ ሴቶችና ወጣቶችን በተሳትፎና በአመራር ሰጭነት በሚያበረታታ መልኩ አልተቀመጡም፡፡ በዚህ ምክንያት በአገሪቱ እስከ መጋቢት 2003 ዓ.ም በህብረት ሥራ ከተደራጁ 6,781,223 አባላት ውስጥ የሴቶች ብዛት 1,322,299 (19.49%) ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡

53. በአገራችን በ35 ዓይነት  የተሠማሩ ህብረት ስራ ማህበራት ቢኖሩም የፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ እስከ 2003 ዓ.ም ለ6ቱ ዓይነት የህብረት ስራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ለ29ኙ (83%) አላዘጋጀም፡፡

54. በናሙና ከታዩ የክልል ኀብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች መካከል በአማራ ክልል ከ6ቱ የአደረጃጀት መመሪያዎች 5ቱ ያልተገኙ ሲሆን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የኀብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ደግሞ 6ቱም መመሪያዎች አልተገኙም፡፡ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአሶሳ ወረዳ ኀብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት የንብ ማነብ፣ የምግብ ዝግጅት፣ የእደ ጥበብ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ኀብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያዎች ሳይኖራቸው ህብረት ስራ ማህበራትን አደራጅተዋል፡፡ በኦዲት ወቅት ከታዩ 8 የወረዳ ኀብረት ሥራ ማህበራት ጽ/ቤቶች መካከል 5ቱ ወረዳዎች ምንም ዓይነት የአደረጃጀት መመሪያ የሌላቸው ሲሆን ሦስቱ ደግሞ

ከፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ብቻ ተሰጥቷቸዋል፡፡

55. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ፣ የአማራ፣ የደቡብ፣ የኦሮሚያ፣ የትግራይ፣ የአዲስ አበባና የድሬደዋ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች በህብረት ስራ ማህበራት የስራ መመሪያዎች አተገባበር ላይ ክትትል አላደረጉም፡፡

56. ለፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ባለሙያዎች ኤጀንሲው የህብረት ስራ ማህበራት በአፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት መስራታቸውን ስለመከታተሉ በቀረበ መጠይቅ ለሕብረት ስራ ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች አተገባበር ዙሪያ እና ስላጋጠሟቸው ችግሮች እስከ 2003 ዓ.ም አንድ ጊዜ ብቻ የተከታተለ ሲሆን በመደበኛነት ክልሎችም ሆኑ ኤጀንሲው እንደማይከታተሉ እና በክትትል በኩል ጉድለት መኖሩን እንዲሁም በአማራ ክልል ብቻ በህብረት ስራ ማህበራት የሴቶች ተሳትፎ በአመራር ሰጪነት 20% እንዲሆን በመመሪያ ላይ መውጣቱን ገልፀዋል፡፡

57. በዚህ ምክንያት ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት ላይ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ እንዲሆን፣ ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ያለአደረጃጀት መመሪያ እንዲሰሩና በአሰራራቸው ላይ ችግር እንዲፈጥር፣ ህብረት ስራ ማህበራት በአዳዲስ አይነት የህብረት ስራ ዘርፍ እንዳይደራጁ እንቅፋት መፍጠሩ ታውቋል፡፡

## የህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኦዲት ስለመደረጉ፤

58. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የህብረት ስራ ማህበራትን ሂሳብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኦዲት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

59. የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በመላ አገሪቱ ለሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሣብ ምርመራ /ኦዲት/ ማድረጊያ ጊዜ ባለመዘርጋቱ ምክንያት ከ2001-2003 ዓ.ም በኤጀንሲው አማካኝነት ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎችና በሀረሪ ክልል ኦዲት ከተደረጉ 32 ኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የ5 ኅብረት ሥራ ማህበራት የ4 ዓመት ሂሣብ በአንድ ጊዜ የተመረመረ ሲሆን የ6 ኅብረት ስራ ማህበራት ደግሞ የ3 ዓመት ሂሣብ በአንድ ጊዜ

ተመርምሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ኦዲተሮች በሶማሌ እና በአፋር ክልል የሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራትን ሂሣብ ዘግተው ኦዲት አድርገዋል፡፡

60. በዚህ ዙሪያ ለኤጀንሲው ባለሙያዎች በቀረበ መጠይቅ በኤጀንሲው ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በአገር አቀፍ አንድ ወጥ የሆነ የኦዲት ማንዋል ተዘጋጅቶ ስልጠና ቢሰጥም ተግባራዊ እንዳልተደረገና ለኦዲት በሚሄዱበት ጊዜ ህብረት ሥራ ማህበራት ቀድመው ሂሳባቸውን ስለማይዘጉ የህብረት ስራ ማህበራትን ሂሣብ ዘግተው ኦዲት እንደሚያደርጉ ገልፀው ይህም ትክክል አለመሆኑን ተቀብለዋል፡፡

61. በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና በሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት (በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ) ከተደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በአጠቃላይ በአማካይ በ2001ዓ.ም 25,155(80.8%)፣ በ2002 ዓም 26,837(77.7%)፣ በ2003 ዓ.ም 31,267(84.2%) ኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት አልተደረጉም፡፡

62. ይህን በተመለከተ ለክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ/ቢሮ (ለአማራ፣ለአዲስ አበባ፣ ለኦሮሚያ እና ለደቡብ) የስራ ኃላፊዎች በቀረበ መጠይቅ ህብረት ስራ ማህበራት በወቅቱ ሂሳባቸውን ባለመዝጋት፣ በቂ ኦዲተር ባለመኖር እና ህብረት ስራ ማህበራት በባለሙያ ባለመመራታቸው ምክንያት የአብዛኛው ህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት እንዳልተደረገ ገልፀዋል፡፡ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲም ኅብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት አለመደረጋቸው ችግር እንደሚፈጥር ይሁን እንጂ ህብረት ስራ ማህበራትን በሙሉ ኦዲት እንደማያደርግ ገልጿል፡፡

63. ይህም በመሆኑ ህብረት ሥራ ማህበራት ወቅቱን ጠብቀው ሂሳባቸው ኦዲት እንዳይደረግ፣ የትርፍ ክፍፍል እንዳያካሂዱ፣ ጠቅላላ ጉባዔ እንዳይጠሩ፣ የብድር አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

## ኤጀንሲውና የሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የሚሰሩትን የኦዲት ሪፖርት ለሕብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አቅርበው በማስፀደቅ በኦዲት ሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነት ስለመከታተላቸው እና የማህበራትን የሂሳብ ምርመራ ውጤት መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ማህበር ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሰርተፊኬት መስጠታቸውን በተመለከተ፡፡

64. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የሕብረት ስራ ማህበራትን የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርበው በማስፀደቅ በኦዲት ሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነት ሊከታተሉ እንዲሁም በሪፖርቱ መሰረት ለእያንዳንዱ ህብረት ስራ ማህበር ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሰርተፊኬት ሊሰጡ ይገባል፡፡

65. የፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ በራሱ ባለሙያዎች የሰራውን የኦዲት ሪፖርት ለሕብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ አላስፀደቀም፣ በኦዲት ሪፖርት የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነትም አልተከታተለም፣ ይህን በተመለከተ ለኤጀንሲው ባለሙያዎች በቀረበ መጠይቅ ኤጀንሲው የሠራውን ኦዲት በአካል ሄዶ ያስፀድቅ እንዳልነበር እና በሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን የመከታተሉ ሥራ አነስተኛ በመሆኑ የተሰሩ የኦዲት ሪፖርቶች ሳይፀድቁ እንደሚቀሩ በመገንዘብ በ2004 ዓ.ም በራሱ ባለሙያዎች ለማስፀደቅ በዕቅድ መያዙን ገልፀዋል፡፡

66. የፌዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ኦዲት ላደረጋቸው የኀብረት ሥራ ማህበራት በኦዲቱ መሠረት ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት አልሠጠም፡፡ በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 4 የክልል ኀብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት 3ቱ /75%/ ለኀብረት ሥራ ማኀበራት የሂሣብ ምርመራ ውጤታቸውን መሠረት በማድረግ ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት እንዳልሰጡ ታውቋል፡፡

67. ከዚህ ጋር በተያያዘ በኦዲት ወቅት ከታዩት የኀብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት በአዲስ አበባ መስተዳድር የየካ ክፍለ ከተማ የኀብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ የሥራ ሂደት ለኀብረት ሥራ ማኀበራት ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት ሠጥተው እንደማያውቁ፣ በዚህ ረገድ ኤጀንሲውም የላከላቸው መመሪያ አለመኖሩንና ግንዛቤው የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን ለክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ/ቢሮ/ ኃላፊዎች በቀረበ መጠይቅ ለኀብረት  ስራ ማህበራት ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት መስጠት አግባብነት ያለው መሆኑን ቢያምኑም በክልል ይሄንን የሚገልፅ መመሪያ ባለመኖሩ ሥራው ሳይሰራ ቀርቷል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

68. ይህም በመሆኑ የኀብረት ሥራ ማህበራት የውድድር መንፈስ እንዳይኖራቸው፣ ያሉበትን ደረጃ እንዳያሻሽሉ፣ ከአበዳሪ አካላት ጋር የበለጠ ተጠናክረው እንዳይሰሩ እንዲሁም በደረጃቸው መሠረት አዳዲስ አባላትን ማፍራት እንዳይችሉ አድርጓል፡፡

## የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁ ማህበራት የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣

69. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁት ሕብረት ስራ ማህበራት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወዘተ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡

70. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁት ሕብረት ስራ ማህበራት በዓመት አንድ ጊዜ በመደበኛነት የኢንስፔክሽን አገልግሎት የማይሰጡ ሲሆን በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በክልል ሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት (በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል እና በደቡብ) የተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት በአጠቃላይ በ2001 ዓ.ም 22,225(71.4%)፣ በ2002 ዓ.ም 20,734(60%)፣ በ2003 ዓ.ም 26,912 (72.5%) በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወዘተ የኢንስፔክሽን አገልግሎት አላገኙም፡፡ እንዲሁም በወረዳና በዞን ደረጃ የሚገኙ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ኢንስፔክት ላደረጓቸው የህብረት ስራ ማህበራት የኢንስፔክሽን ግብረ መልስ እንደማይልኩ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

71. በዚህ ዙሪያ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ/ቢሮ(አማራ፣ ኦሮሚያ፣ አዲስ አበባ፣ ደቡብና ቤኒሻንጉል) ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ በሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት እና በህብረት ስራ ማህበራት ቁጥር ከፍተኛ መሆን ምክንያት አብዛኞቹ ህብረት ስራ ማህበራት ኢንስፔክት እንዳልተደረጉ የገለፁ ሲሆን የፌዴራል ህብረት ስራ ኃላፊዎችም ተጠይቀው ኤጀንሲው የሰው ሃይል ባለመኖሩ ምክንያት የኢንስፔክሽን ስራ በቅርቡ ማድረግ እንደጀመረ ገልጿል፡፡ እንዲሁም ያደራጀውን መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር በ2003 ዓ.ም ኢንስፔክት እንዳደረገ ቢገልፅም የኢንስፔክሽን ግብረ መልሱ እስከ ኦዲቱ ማብቂያ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

72. በዚህም የተነሳ የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የማህበራትን ጠንካራና ደካማ ጎን በማወቅ ድጋፍ እንዳይሰጡና ችግሮቻቸው በወቅቱ መፍትሔ እንዳያገኝ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡

## የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት በህብረት ስራ ጠቀሜታ፣ እንቅስቃሴና ዕድገት ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠራቸውን በተመለከተ፣

73. ኤጀንሲው እና የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በሕብረት ስራ ጠቀሜታ፣እንቅስቃሴና እድገት ዙሪያ ለተደራጅዎችና ለባለድርሻ አካላት በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ ሊፈጥሩ ይገባል፡፡

74. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ስለ ሕብረት ስራ ጠቀሜታ፣ እንቅስቃሴ እና እድገት ለተደራጅዎችና ለባለድርሻ አካላት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ባለመፍጠራቸው በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩት 30 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በፌዴራል፣ በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባና በቤኒሻንጉል 10 ህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም በሶማሌ እና በአፋር የተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት ቀድመው ስለህብረት ስራ ማህበር ምንነት እና ጠቀሜታ በቂ ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡

75. ስለ ጉዳዩ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ለህብረት ስራ ማህበራት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ባለመፈጠሩ እና ከመደራጀታቸው በፊት ስለ ህብረት ስራ ጠቀሜታ ግንዛቤ ከማጣት ችግር እንቅስቃሴያቸው ደካማ መሆኑን እንዲሁም የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የስራ ሃላፊዎችም ተጠይቀው ኤጀንሲው ስለህብረት ስራ ማህበራት ለባለድርሻ አካላት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን እንዳልፈጠረ ገልጸዋል፡፡

76. ይህም በመሆኑ ህብረተሰቡ በህብረት ስራ ላይ ያለው ተሳትፎ እንዳይጨምርና ተጠቃሚ እንዳይሆን፣ህብረት ሥራ ማህበራት በአሰራራቸው ዙሪያ በቂ እውቀት እንዳይኖራቸውና ከባለድርሻ አካላትም ሆነ ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች ማግኘት ያለባቸውን ድጋፍ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል፡፡

### 2.2 የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በደንቡ መሠረት የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ መሆኑንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

### የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ ማድረጉን እንዲሁም ህብረት ስራ ማህበራት የምርትና የገበያ ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ መደበኛ የሆኑ የመወያያ መድረኮች ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

77. ኤጀንሲው የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ እገዛ (የገበያ ቦታ፣ ገዥዎችን በማፈላለግ፣ ስለገበያ መረጃ በመስጠትና የእርስ በእርስ ገበያ ትስስር በመፍጠር) ሊያደርግና በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራት የምርትና የገበያ ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ መደበኛ የሆኑ የመወያያ መድረኮች (ወርክሾፕ፣ ሴሚናር ወዘተ) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

78. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ የመስጠት፣ በሀገር ውስጥ ሸማችና አምራች በቀጥታ የሚገናኙበትን ሁኔታ የማመቻቸት ስልጣን በአዋጅ የተሰጠው ቢሆንም ከህዳር 1/2001 ዓ.ም ጀምሮ ማንኛውንም ግብይትን የተመለከተ አገልግሎት ለኅብረት ሥራ ማህበራት መስጠት ማቋረጡን ለመረዳት ተችሏል፡፡

79. የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን አለማመቻቸቱ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በአዲስ አበባና በቤኒሻንጉል ክልል የሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የገበያ መረጃ እንዳያገኙ፣ የሚያመርቱት ምርት በሚፈለገው ቦታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዳይሸጥ፣ ለህገ ወጥ የገበያ ስርዓት እንዲጋለጡ፣ አምራችና ተጠቃሚ በቀጥታ እንዳይገናኙ ማድረጉ እንዲሁም ከአምራቾች፣ ጅምላ አከፋፋዮች፣ አስመጪና ላኪዎች ጋር ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር ፈጥሮ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል መድረክ እንዳይኖር አድርጓል፡፡

80. ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩና የሰርቬይ መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 37 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በቤኒሻንጉልና በፌዴራል 13ቱ (35%) ከ2001-2003 ዓ.ም የምርትና የገበያ የልምድ ልውውጥ አግኝተው የማያውቁ ሲሆን 19ኙ (51.3%) ህብረት ስራ ማህበራት ደግሞ

በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በክልሎች በሚዘጋጀው የህብረት ስራ ቀን በዓል ላይ እስከ 2003 ዓ.ም አንድ ጊዜ የተሳተፉ ቢሆንም ምርታቸውን ከማስተዋወቅ ውጭ የምርትና የገበያ የልምድ ልውውጥ እንዳልተደረገላቸው ተረጋግጧል፡፡

81. በዚህ ዙሪያ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው ማህበራት በተደራጁበት በየትኛውም ዓይነት ዘርፍ የገበያ ማስፋፋትና የገበያ ማገናኘት ስራ የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ተግባር አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ የግብርና ምርት ግብይትን በተመለከተ በንግድ ሚኒስቴር እየተሰራ ቢሆንም በሌሎች የህብረት ስራ ዘርፎች ግን በግብርናም ሆነ በንግድ ሚኒስቴር ስለመሰራቱ የተገኘ መረጃ የለም፡፡

82. የገበያ ድጋፍና የልምድ ልውውጥ ባለመደረጉ ህብረት ስራ ማህበራት የሚያመርቱትን ምርት በሚፈለገው ቦታ እና በጥሩ ዋጋ እንዳይሸጡ፣ እቃዎችን በውድ ዋጋ ከነጋዴዎች በመረከብ ለመሸጥ እንዲገደዱ፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት መጋዘን የተከማቸ ሰብል ባለመሸጡ ለብልሽትና ለኪሣራ እንዲዳረጉ እንዲሁም የሌሎችን መልካም ተሞክሮ በመቅሰም ያሉባቸውን ችግሮች በመቅረፍ በተሰማሩበት ዘርፍ ብቁ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

## የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲና በየደረጃው የሚገኙ የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ተቀናጅተው የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት እንዲኖራቸው እና ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ እንዲሁም የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ እገዛ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤

83. የህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በየደረጃው የሚገኙ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ተቀናጅተው የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት/ዋጋ እንዲኖራቸው እና ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ እንዲሁም የህብረት ስራ ማህበራት የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

84. ኤጀንሲው እና በየደረጃው የሚገኙ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በጋራ በመሆን የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት/ዋጋ/ እንዲኖራቸው እና በሚፈለገው ቁጥር ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ አላደረጉም፡፡ በኦዲቱ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተደራጁት 6,781,223 አባላትን የያዙና 3,884,299,411 ካፒታል

ያሏቸው 38,699 መሰረታዊና ዩኒየን የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ እስከ 2003 ዓ.ም መጨረሻ ወደ አግሮ ኢንዱስትሪነት የተቀየሩ 29 (ከ1% ያነሱ) ህብረት ስራ ማህበራት ብቻ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

85. ይህንን በተመለከተ የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ተጠይቆ ቡና መፈልፈያና ማጠቢያ ኢንዱስትሪ ያላቸው የህብረት ስራ ማህበራት ከተጨመሩ ቁጥራቸው ከ29 በላይ እንደሚሆን ቢገልፅም እስከ ኦዲቱ መጨረሻ ማስረጃውን ለኦዲት ቡድኑ አላቀረበም፡፡

86. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ 2002 ዓ.ም መጨረሻ ከተደራጁት ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 70 በመቶ ያህሉን የብድር ተጠቃሚ ለማድረግ እቅድ ቢይዝም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት መካከል 17 ህብረት ስራ ማህበራት የብድር አገልግሎት ለማግኘት የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላትን ድጋፍ ቢጠይቁም 8ቱ (47 በመቶ) ከ2001-2003 ዓ.ም የብድር ተጠቃሚ አልሆኑም፡፡

87. ስለ ጉዳዩ የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ብድር እንዲያገኙ የማመቻቸት ተግባር ከግብይት ስራ ጋር የሚጠቃለልና የክልል ማስፋፊያ አካላት ስራ በመሆኑ በኤጀንሲው አገልግሎቱ አለመሰጠቱን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በዚህ ረገድ ክትትል በማድረግ የወሰደው እርምጃ የለም፡፡ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ሃላፊዎች ተጠይቀው ማህበራት ብድር እንዲያገኙ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

88. ይህም በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች የተሻለ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል መልኩ እንዳይለወጡና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዳይቀርፉ ማድረጉ እንዲሁም ብድር እንዲያገኙ የፌደራል እና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ሁኔታዎችን ባለማመቻቸታቸው ህብረት ስራ ማህበራት ስራ እንዳይጀምሩና እንቅስቃሴያቸውን አስፋፍተው ካፒታላቸውን ማሳደግ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፡፡

**የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ከማስፋፊያ አካላትና ከማህበራት ጋር ሪፖርቶችን፣ ጥናቶችን፣ ህትመቶችን፣ መመሪያዎችንና መረጃዎችን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደሚለዋወጥ እንዲሁም ከማስፋፊያ አካላት ጋር በሪፖርት አደራረግ፣ በስልጠና አሰጣጥና ስልጠናው ያመጣው ውጤት አለካክ ዘዴና ቁጥጥር ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of Understanding) መፈራረሙን እና መረጃዎችን በዳታ ቤዝ ስርዓት በማስደገፍ መያዙን በተመለከተ፣**

89. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ ከማስፋፊያ አካላትና ከማህበራት ጋር ፈጣን የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ በመጠቀም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሪፖርቶችን፣ ጥናቶችን፣ ህትመቶችን፣ መመሪያዎችንና መረጃዎችን ሊለዋወጥ እንዲሁም ከማስፋፊያ አካላት ጋር በሪፖርት አደራረግ፣ በስልጠና አሰጣጥና ስልጠናው ያመጣው ውጤት አለካክ ዘዴ ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ (MoU) ሊፈራረም እና በዳታ ቤዝ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

90. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ አገር አቀፍ የህብረት ስራ መረጃ ስብሰባ፣ ትንተና እና ስርጭት የአሰራር ስርዓት ሲያዘጋጅ ከፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ወደ ክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች፣ ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ወደ ዞን፣ ከዞን ወደ ወረዳ፣ ከወረዳ ወደ ህብረት ስራ ማህበራት መረጃ የሚደርስበትን ቀን ባዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ ባለማስቀመጡ በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የተዘጋጁ ሪፖርቶች፣ ጥናቶች፣ ህትመቶችና መመሪያዎች ወደ ክልሎች ሲላኩ እስከ 3ወር እንደሚዘገዩ እንዲሁም ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት መረጃዎች በየሩብ ዓመቱ የመጨረሻ ቀን ለኤጀንሲውና ለባለድርሻ አካላት መሰራጨት እንዳለባቸው በጊዜ ሰሌዳው የተጠቀሰ ቢሆንም የዕቅድና ክንውን ሪፖርቶች ለፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የሚላኩት እስከ 34 ቀናት ዘግይተው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

91. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ኤጀንሲው በሀገሪቱ ያሉትን የእያንዳንዱን ህብረት ስራ ማህበራት ስም ዝርዝር፣ የተመዘገቡበት ቀን፣ ያስመዘገቡት የካፒታል መጠንና በስራ ላይ ያሉትን የሚገልፅ መረጃ በዳታ ቤዝ ይዞ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአዲስ አበባ እና በቤኒሻንጉል ክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች በዞን እና በወረዳ ደረጃ የተመዘገቡ ህብረት ስራ ማህበራት መረጃ በተሟላ ሁኔታ አልተገኘም፡፡

92. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ጋር በድጋፍ አሰጣጥ ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ (MoU) የለውም፡፡

93. ይህንንም በተመለከተ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ተጠይቆ ከኤጀንሲ ወደ ማስፋፊያ አካላት መረጃዎች የሚሰራጩበት ጊዜ በሰሌዳው አለማስቀመጡን በዚህም ምክንያት ለክልሎች መረጃዎች በወቅቱ እንዳልደረሱ፣ ክልሎችም በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ ለኤጀንሲው እንደማይልኩ እና በዳታ ቤዝ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመዘርጋቱንም የገለፁ ሲሆን ከክልል ማስፋፊያ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ የሚል መመሪያ አለመኖሩን እና የመግባቢያ ሰነድ እንደሌላቸው ይሁን እንጅ ለወደፊቱ ጠቀሜታው ታይቶ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

94. የመግባቢያ ሰነድ (MoU) ባለመኖሩ ምክንያት በሪፖርት አደራረግ፣ በስልጠና አሰጣጥና ስልጠናው ያመጣው ውጤት አለካክ ዘዴና ቁጥጥር በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት እንደሆነ እንዲሁም በዳታ ቤዝ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ የህብረት ሥራ ማህበራትን በቀላሉ ለመከታተልና ድጋፍ ለመስጠት አላስቻለም፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

95. የህብረት ስራ ማህበራትን ለማደራጀት፣ ለመደገፍና ውጤታማ ለማድረግ በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በክልል ማስፋፊያ አካላት የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ የዚህ ክዋኔ ኦዲት ዓላማ ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት በአግባቡ መፈፀሙንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር የአሰራር ስርዓቱ አፈፃፀምና ውጤታማነት በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ያሉበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

96. ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ እንዲቀረፅ አለማድረጉ፤ ይህም ፖሊሲ ባለመኖሩ ምክንያት የህብረት ስራ ማህበራት አቅጣጫና ዕድገት አመላካች እንዳይኖር፣ የህብረት ስራ ማህበራትን እድገት ለመለካት አስቸጋሪ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን መስተጋብር ለይቶ ለማወቅ አዳጋች ማድረጉ፤

97. ኤጀንሲው ከ2000-2002 ዓ.ም እና ከ2003-2007 ዓ.ም ባዘጋጃቸው ስትራቴጂክ ዕቅዶች 2204 መጋዘኖች ተገንብተው ለማህበራት ድጋፍ እንደሚሰጡ አቅዶ በእቅዱ መሰረት አለመከናወኑ፤ ከ2000-2002 ዓ.ም ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ የህብረት ስራ ባንኮችን፣ ኢንሹራንሶችን፣ ፌዴሬሽኖችን ለማደራጀትና የገበያ ትስስር ለመፍጠር ቢያካትትም በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ፤ በየጊዜው በሚያዘጋጀው የእቅድ ክንውን ሪፖርት መሰረት ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ አለመውሰዱ፤

98. ኤጀንሲው ክልሎች የአዋጭነት እና የሶሽዩ ኢኮኖሚ ጥናት እንዲያጠኑ በተግባር በማሳየት እገዛ አለማድረጉና በክልሎች የሚጠናው የአዋጭነት ጥናት ወጥነት የሌለው መሆኑ እንዲሁም ባህላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት ወደ ዘመናዊ ህብረት ስራ የሚያድጉበትን ጥናትና ምርምር አለማድረጉ፤

99. ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ሥራ ፌዴሬሽን እና የህብረት ስራ ሊግ አለማቋቋሙ፤ እንዲሁም ከክልል ሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች የሕብረት ስራ ማህበራትን በመሰረታዊ እና በዩኒየን እንዲደራጁ ያደረገው እገዛ ከ2001- 2002 ዓ.ም ዝቅተኛ ሲሆን በሌሎች ክልሎች እንዲደራጁ እገዛ ያደረገበት ማስረጃ አለመገኘቱ፣

100. ኤጀንሲው ካዘጋጃቸው 20 መመሪያዎች ውስጥ ለክልሎች አስር መመሪያዎች ብቻ የላከ እና የክልል ማስፋፊያ አካላት እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ማሻሻያ ያላደረጉ መሆናቸው፤

101. በህብረት ስራ አዋጅና ደንብ ላይ የተቀመጡት የማህበራት ማበረታቻዎች (ቦታ የማግኘት፣ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆንና ያለ ኢንቨስትመንትና ያለ ንግድ ፈቃድ መስራት) ምላሽ ሊያገኙ በሚችሉበት ሁኔታ በመመሪያዎች ላይ በግልፅ አለመቀመጡ እንዲሁም ያለንግድ ፈቃድ የመስራት ማበረታቻ ከአዲሱ የንግድ ሚኒስቴር አዋጅ ቁጥር 686/2002 ጋር እንዲስማማ የተደረገ ጥረት አለመኖሩ፤

102. ሴቶችና ወጣቶች በህብረት ስራ ማህበራት ላይ እንዲሳተፉ በሚያበረታታ መልኩ በተዘጋጁት መመሪያዎች ውስጥ አለመካተቱ፤ በእያንዳንዱ ዓይነት የማኀበራት አደረጃጀት ዘርፍ የአደረጃጀት መመሪያ አለመዘጋጀቱ ወይም ወጥ የሆነ ለሁሉም ዘርፍ የሚያገለግል አለማዘጋጀቱ እና የተዘጋጁትንም አለማሠራጨቱ፤ እንዲሁም የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት በደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች አተገባበር ዙሪያ ህብረት ስራ ማህበራትን አለመከታተላቸው፤

103. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ የህብረት ስራ ማህበራት ማሰልጠኛ ተቋም ያላቋቋመና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለባለሙያዎችና ለኀብረት ሥራ ማህበራት ለሚሠጡት ስልጠና የስልጠና ፍላጐት ጥናት እንደሚያደርጉ አለመከታተሉ፣ እንዲሁም የስልጠና ፍላጐት ጥናት አለመጠናቱ እና ለሰጠው ሥልጠና የስልጠናውን ውጤት ለመለካት የሚያስችል የመለኪያ አሠራር አለመኖሩ፤

104. የፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ በመላ አገሪቱ ለሚገኙ ኀብረት ሥራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሣብ ምርመራ /ኦዲት/ ሥርዓት አለመዘርጋቱና መደበኛ የሆነ የኦዲት ማድረጊያ ጊዜ አለመኖሩ፤ እንዲሁም በኤጀንሲውና በሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት (በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣በኦሮሚያ እና በደቡብ) የተደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት በአማካይ በ2001 ዓ.ም 80.8%፣ በ2002 ዓ.ም 77.7%፣ በ2003 ዓ.ም 84.2% ኀብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት አለመደረጋቸው፡፡

105. የፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ የሠራቸውን የኦዲት ሪፖርቶች ለኀብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ አለማስፀደቁና በኦዲት ሪፖርት የተሰጡ አስተያየቶች

ተግባራዊ መሆናቸውን አለመከታተላቸው፤ እንዲሁም ኤጀንሲውና የክልል ህብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ለኀብረት ስራ ማህበራት በኦዲት ሪፖርታቸው መሠረት ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት አለመስጠታቸው፤

106. በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ፣ በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ከተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በ2001 ዓ.ም 71.4%፣ በ2002 ዓ.ም 60%፣ በ2003 ዓ.ም 72.5% በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወዘተ የኢንስፔክሽን አገልግሎት አለማግኘታቸው።

107. በፌዴራል፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል፣ በአፋር እና በሱማሌ ክልሎች የተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት በህብረት ስራ ጠቀሜታ፣ እንቅስቃሴና ዕድገት ዙሪያ ግንዛቤ ሳያገኙ መደራጀታቸው እንዲሁም የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና የክልል ማስፋፊያ አካላትም በዚህ ዙሪያ ለህብረት ስራ ማህበራትም ሆነ ለባለድርሻ አካላት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን አለመፍጠራቸው፤

108. በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጠው የግብይት ድጋፍ ከህዳር 1/2001 ዓ.ም ጀምሮ መቋረጡ፤ እንዲሁም ህብረት ስራ ማህበራት መደበኛ የሆነ የልምድ ልውውጥ እንዲኖራቸው አለመደረጉ፤

109. በአገር አቀፍ ደረጃ ከተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ እስከ 2003 ዓ.ም ወደ ኢንዱስትሪነት የተለወጡት ከ1 በመቶ በታች መሆናቸው፤

110. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ሪፖርቶችን፣ ጥናቶችን፣ ህትመቶችን፣ መመሪያዎችንና መረጃዎችን ለመላክ የሚያስችል የጊዜ ገደብ ያላስቀመጠ ሲሆን የእያንዳንዱን የህብረት ስራ ማህበራት ስም ዝርዝር፣ የተመዘገቡበት ቀን፣ የካፒታል መጠናቸውንና በስራ ላይ ስለመሆናቸው የሚገልፅ መረጃ በኤጀንሲውም ሆነ በክልል ማስፋፊያ አካላት አለመገኘቱ። ከዚህ በተጨማሪም ኤጀንሲው ከማስፋፊያ አካላት ጋር በሪፖርት አደራረግ፣ በስልጠና አሰጣጥና ስልጠናው ያመጣውን ውጤት አለካክ ዘዴና ቁጥጥር ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) አለመኖሩ፤

111. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል።

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

112. ህብረተሰቡ ስለ ህብረት ሥራ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረውና ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ እንዲሁም ለህብረት ስራ ማህበራት አቅጣጫ እና ዕድገት አመላካች እንዲሆን የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

113. ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የስትራቴጅክ ዕቅድ ውስጥ ለማህበራት በሚሰጠው ድጋፍ ዙሪያ የሚሰራውን ሥራ በማካተት ተግባር ላይ መዋላቸውን ሊከታተል፣ በስትራቴጂክ ዕቅድ የተካተቱ ተግባራትን በዓመታዊ ዕቅድ በመያዝ ሊያከናውን እንዲሁም በየበጀት ዓመቱ ላልተከናወኑ ተግባራት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

114. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ማህበራት ከተደራጁ በኋላ ለመፍረስና ለኪሳራ እንዳይጋለጡ፣ለአባሎቻቸውና ለህብረተሰቡ ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴያቸውን ለመገምገም እንዲያስችል እና ውጤታማ ለመሆን የሚያስችላቸውን የህብረት ስራ ዘርፍ ለመምረጥ ከመደራጀታቸው በፊት የሶሽዩ ኢኮኖሚ ጥናትና የአዋጭነት ጥናት ሊያጠና ወይም ክልሎች እንዲያጠኑ እገዛ ሊያደርግ እንዲሁም በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት የማህበራትንና የአባላትን አቅም ለማጎልበትና የአሰራር ስርአታቸውን ለማሻሻል በባህላዊና ሀገር በቀል ደረጃ ያሉትን እድር መረዳጃ ማህበራት ወዘተ ወደ ዘመናዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናትና ምርምር ሊያደርግ ይገባል፡፡

115. የህብረት ስራ ማህበራት ለአባላቶቻቸው እና ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት መፋጠን የሚያበረክቱትን አስተዋጽዖ በተሻለ ደረጃ ለመወጣት እና ከአለም አቀፍ የሕብረት ሥራ ማህበራት ጋር በማስተሳሰር የማህበራትንና የአባላትን አቅም ማሳደግ እንዲያስችል በአገር አቀፍ ደረጃ የሕብረት ሥራ ፌዴሬሽንና የህብረት ስራ ሊግ ሊያቋቁም ይገባል፡፡

116. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የህብረት ስራ ማህበራትን አቅም ለማጎልበት፣ በፌዴራል እና በክልል የሚሰጡ ስልጠናዎችን ተመጋጋቢ ለማድረግ፣ የስልጠና ድግግሞሽን ለማስቀረት እና የሚሰጡ ስልጠናዎች የሚያመጡትን ውጤት ለመለካት ተናበው ሊሠሩ ይገባል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው የስልጠና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ለሚሰጡት ስልጠና የስልጠና ፍላጐት ጥናት እንደሚያደርጉ ሊከታተልና በየጊዜው የሚሠጡ ስልጠናዎች በሠልጣኙ እና በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ያመጡትን ውጤት ለማወቅና ለቀጣይ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ለማቀድ እንዲያስችል ስልጠናዎች ያመጡትን ውጤት የሚገመግምበትና የሚለካበት ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

117. በህብረት ስራ አዋጅና ደንብ ላይ ማህበራት የማበረታቻ (ቦታ የማግኘት፣ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን፣ ያለ ኢንቨስትመንትና ንግድ ፈቃድ መስራት) ምላሽ ሊያገኝ በሚችልበት ሁኔታ በመመሪያዎች ላይ በግልፅ በማስቀመጥ እንዲሁም ይህ ማበረታቻ (ከግብር ነፃ የመሆንና ያለንግድ ፈቃድ መስራት)ንግድ ፈቃድን በተመለከተ ከአዲሱ የንግድ ሚኒስቴር አዋጅ ቁጥር 686/2002 ጋር እንዲስማማ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፤

118. ሴቶችና ወጣቶች በህብረት ስራ ማህበራት ያላቸውን ተሳትፎ ለማበረታታት፣ ቁጥራቸውንና በአመራር ሰጪነት ተሳትፏቸውን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ በመመሪያዎች ውስጥ ሊካተት እና በእያንዳንዱ ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፍ ወይም ሁሉንም ህብረት ስራ ማህበራት የሚመለከት ወጥ የሆኑ የአደረጃጀት መመሪያዎችን እንዲሁም መመሪያ ላልተዘጋጀላቸው በማዘጋጀት፣ በማሠራጨት እና ተግባራዊነቱን በመከታተል በየክልሉ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ አካላት አዳዲስ አይነት ኅብረት ስራ ማህበራትን እንዲያደራጁ ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም ማህበራት በደንብ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ስለመሰራታቸውና በስራ ላይ ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመቅረፍ እንዲያስችላቸው ኤጀንሲውና የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለችግሮቻቸው የመፍትሔ ሃሳብ በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ ሊከታተሉ ይገባል፡፡

119. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራት ሂሳብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲመረመር እና ተአማኒነት ያለው ኦዲት ለማድረግ እንዲያስችል ለህብረት ስራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ስርዐት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

120. የህብረት ሥራ ማህበራት የትርፍ ክፍፍል እንዲያደርጉና ያሉበትን ደረጃ በማወቅ የበለጠ እንዲሠሩ የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲና የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ኅብረት ሥራ ማህበራትን በየአመቱ ኦዲት በማድረግ ወይም በተወካይ ኦዲት እንዲደረጉ እገዛ በማድረግ የኦዲት ሽፋንን ማሳደግ ይገባል፡፡

121. የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ እና የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት የሚሰሩትን የኦዲት ሪፖርት ለኅብረት ሥራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባዔ አቅርበው ሊያስፀድቁና በሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነት ሊከታተሉ ይገባል፡፡

122. የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲና የክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት በሂሣብ ምርመራ ወቅት አስቀድሞ በተቀመጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ መስጫ መመዘኛ ነጥቦች (የኅብረት ሥራ ማህበሩ የአባላት እድገት መጠን፣ የካፒታል ዕድገት መጠን፣ የብድር አወሣሠድና አመላለስ፣ የገንዘብና ንብረት አጠባበቅ፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ትርፋማነት ወዘተ) መሠረት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት በመስጠት ኅብረት ሥራ ማህበራት የውድድር መንፈስ እንዲፈጥሩ፣ ተጨማሪ አባላትን ማፍራት እንዲችሉ እንዲሁም ከአበዳሪ አካላት ጋር የበለጠ ተጠናክረው እንዲሠሩ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

123. ኤጀንሲውና የሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት የህብረት ስራ ማህበራትን ጠንካራ እና ደካማ ጎን በማወቅ ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም በመመሪያ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የኢንስፔክሽን ማንዋል በማዘጋጀት የተደራጁ ሕብረት ስራ ማህበራትን በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወዘተ ኢንስፔክት አድርገው የኢንስፔክሽን ግብረ-መልስ ሊሰጧቸው እና በማሻሻያው ሃሳብ መሰረት ስለመስራታቸው ሊከታተሉ ይገባል፡፡

124. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራት ከመደራጀታቸው በፊት ስለ ህብረት ስራ ማህበር ጠቀሜታ፣ እንቅስቃሴና ዕድገት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ የሚገባቸውን ድጋፍ ማግኘት እንዲያስችላቸው፣ እንቅስቃሴያቸውን ይበልጥ ለማጎልበት፣ ባለድርሻ አካላት ስላላቸው ሚና እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ማግኘት የሚፈልጉትን እገዛ በቀላሉ እንዲያገኙ በክልል ካሉት የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ጋር በጋራ በመሆን የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎችን (በመገናኛ ብዙሃን፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕና በመወያያ መድረኮች ወዘተ) በመጠቀም ለህብረት ስራ ማህበራት እና ለባለድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ ሊያስጨብጡ ይገባል፡፡

125. የህብረት ስራ ማህበራት ከገበያ እንዳይወጡ፣ ምርታቸውን ወደ ሌላ ቦታ ሄደው መሸጥ እንዲችሉ፣ የሌሎችን መልካም ተሞክሮ እንዲቀስሙ፣ ያለባቸውን ችግሮች በመቅረፍ በተሰማሩበት ዘርፍ ብቁ ለማድረግ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ የገበያ ቦታና ገዥዎችን በማፈላለግ፣ ስለ አገር ውስጥና የውጭ አገር ገበያ መረጃ በመስጠት፣ የእርስ በእርስ ገበያ ትስስር በመፍጠር ድጋፍ ሊሰጥ እና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተደራሽ በሆነ መልኩ ለህብረት ስራ ማህበራት የምርትና የገበያ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

126. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በየደረጃው የሚገኙ የህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ከሚመለከታቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመሆን የህብረት ስራ ማህበራት የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ብድር የሚያገኙበትን ስርዓት በመዘርጋት፣ ለህብረት ስራ ማህበራት በብድር አወሳሰድና አመላለስ ዙሪያ ግንዛቤ በማስጨበጥ፣ እንዲሁም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ተቋማት ተደራሽ እንዲሆኑ እገዛ በማድረግ የህብረት ስራ ማህበራት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተው ሲገኙ የብድር ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አደረጃጀታቸውን በማጠናከር እና ችግሮቻቸውን በመቅረፍ፣ የህብረት ስራ ማህበራትን ካፒታል ለማሳደግ ከሚያመርቱት ምርት ላይ ተጨማሪ እሴት/ዋጋ/ በመጨመር ምርቶቻቸው ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል፡፡

127. ኤጀንሲው የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በመመሪያዎች፣ በተጠኑ ጥናቶች፣ በህትመቶችና በሪፖርቶች አሰራራቸውን ይበልጥ ለማጠናከር እና መረጃዎችን ለታለመላቸው አላማ ለማዋል እንዲያስችላቸው እንዲሁም ኤጀንሲው መረጃዎችን ለመላክ

ከህብረት ስራ ማህበራት እስከ ባለድርሻ አካላት የሚደርስበትን ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ ህብረት ስራ ማህበራት ለሚሄደው መረጃ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ፈጣን የመረጃ ዘዴን (የኢሜል፣ የፋክስ፣ የፖስታ ወዘተ) በመጠቀም መረጃዎችን ሊለዋወጥ እና መረጃዎችን በተፈለገ ቦታና ጊዜ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ከህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ጋር በመሆን በዳታ ቤዝ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋ እንዲሁም ከክልሎች ጋር ሪፖርቶችን በወቅቱ እንዲለዋወጥ፣ ስልጠናዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲሰጡ ወዘተ የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡

አባሪ1

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲትጭብጦች<br>(Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች<br>(Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| 1. ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የወጡ የኤጀንሲው አዋጆች እና የሕብረት ስራ ደንቦችን ተፈጻሚ እና ውጤታማ ለማድረግ ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርአት እንዲሁም የክትትል ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ | 1. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 274/1994 መሰረት የህብረት ስራ ማህበራትን ደንብ እና አዋጅ ተፈጻሚነት ለመከታተል እና አላማውን ለማስፈጸም የሚረዳ በሰው ኀይል የተሟላ አደረጃጀት ሊፈጥር ይገባል፡፡ |
| 1.1 የህብረት ስራ ማህበራት ሲደራጁ በጥናት ላይ ተመስርተው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሚሰራ እና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ የሚደረጉ መሆኑን ማረጋገጥ፡ | 2. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 3. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በሚያዘጋጀው የስትራቴጅክ ዕቅድ ውስጥ ለህብረት ስራ ማህበራት በሚሰጠው ድጋፍ ዙሪያ የሚሰራውን ሥራ ሊያካትትና ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 4. የፌ/ህ/ስ/ኤጀንሲ በአገር አቀፍ ደረጃ የህ/ስራ ፖሊሲ ቀርጾ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 5. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት ዓመታዊ እቅድ ሊያዘጋጅ፣ እቅዱን ተግባራዊ በማድረግ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 6. ኤጀንሲው በየጊዜው በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት መሰረት ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 7. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ ማህበራት ሲደራጁ የአዋጭነት |

| የኦዲትጭብጦች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| | ጥናት ሊያጠና እንዲሁም የክልል ህብረት ስራ ማህበራት ሲደራጁ የአዋጭነት ጥናት እንዲያጠኑ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 8. ኤጀንሲው ማህበራት ከመደራጀታቸው በፊት የሶሽዮ ኢኮኖሚ ጥናት ሊያደርግ እና የክልል ማስፋፊያ አካላት እንዲያደርጉ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 9.የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት/እድር፣መረዳጃ ማህበር ወዘተ/ ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናት እና ምርምር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 10. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እንደየህብረት ስራ ማህበራቱ አይነት እና ደረጃ የማህበራት የመተዳደሪያ ደንብ ሞዴል አዘጋጅቶ ለክልል ህ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ሊያሰራጭና እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ማሻሻያና ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 11.ኤጀንሲው ለህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ አሰጣጥን በተመለከተ የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 12. የሕ/ስ/ማህበራት ደንብና መመሪያዎች ሲዘጋጁ ሴቶችንና ወጣቶችን ሊያበረታታ በሚያስችል መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 13. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ (መሰረታዊ ህ/ስ/ማህበራት፣ ዩኒየንና ፌዴሬሽን) ህ/ስ/ማህበራትን ማደራጀት አለበት፡፡ |
| | 14. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከክልል ሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ሊያደራጅ እና በሌሎች ክልሎች የሕ/ስ/ማህበራትን በመሰረታዊ እና በዩኒየን እንዲደራጁ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 15. ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ የሕብረት ስራ ሊግ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ |
| | 16. ኤጀንሲው ለሕ/ስ/ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ አዘጋጅቶ ለክልል ማስፋፊያ አካላት በመላክ በጥቅም ላይ ማዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| 1.2 ኤጀንሲው ለፌዴራል እና ለክልል ህብረት ስራ ማህበራት የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የአቅም ግንባታ እና የፋይናንስ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፡ | 17. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በፌዴራል ደረጃ የህብረት ስራ ማሰልጠኛ ተቋም ሊያቋቁም፣ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |

| የኦዲትጭብጦች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria's) |
| --- | --- |
| | 18. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ የስልጠና ድጋፍ ከመስጠቱ በፊት የስልጠና ፍላጎት ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 19. የፌዴራል ህ/ስ/ኤጀንሲ ለክልል ህ/ስ/ማስፋፊያ አካላት አመራሮች፣ አሰልጣኞች፣ ባለሙያዎችና ህ/ስ/ማህበራት በሂሳብ አያያዝ፣ በሕግ ጉዳዮች ወዘተ ዙሪያ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 20. የክልል ሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ለአመራሮች፣ ለባለሙያዎችና ለህ/ስ/ማህበራት በቁጥጥር፣ በሂሳብ አያያዝ እና በሕግ ጉዳዮች ወዘተ ዙሪያ ለሚሰጡት ስልጠና የስልጠና ፍላጎት ጥናት እንደሚያደርጉ የፌ/ህ/ስ ኤጀንሲ ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 21. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ በመላ ሀገሪቱ ለሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ስርዐት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 22.የህብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ህ/ስ/ማስፋፊያ አካላት የተደራጁ ህ/ስ/ማህበራትን ሂሳብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሊመረምሩ ይገባል፡፡ |
| | 23. ኤጀንሲውና ሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ህ/ስ/ማህበራት በተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ለማስመርመር ያቀረቡትን ጥያቄ መርምረው በአንድ ቀን ውስጥ ፈቃድ ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 24. ኤጀንሲውና የሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት የኦዲት ሪፖርቱን ለሕ/ስ/ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አቅርበው ሊያፀድቁና በኦዲት ሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነትም ሊከታተሉ ይገባል፡፡ |
| | 25. ኤጀንሲው እና የሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት የማህበራትን የሂሳብ ምርመራ ውጤት መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ማህበር ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ሰርተፊኬት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 26. የፌ/ህ/ስ ኤጀንሲና የክልል ማስፋፊያ አካላት የህ/ስ/ማህበራት የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ/እገዛ ሊያደርጉ ይገባል:: |
| | 27. ኤጀንሲው የህ/ስ/ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ (የገበያ ቦታ፣ገዥዎችን በማፈላለግ፣ ስለ ገበያ መረጃ በመስጠት እና የእርስ በእርስ ገበያ ትስስር በመፍጠር) ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 28.የክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች ለህ/ስ/ማህበራት የቴክኒክ እና የሙያ ስልጠና መስጠታቸውን የፌ/ህ/ስ/ኤጀንሲ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 29. በፌ/ህ/ስ/ኤጀንሲ፣ በክልል ማስተባበሪያ ቢሮዎች፣ኤጀንሲዎች እና ጽ/ቤቶች ለህ/ስ/ማህበራት የሚሰጠው ስልጠና ያመጣው ውጤት የሚለካበት ስርአት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 30. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለህ/ስ/ማህበራት ስለሚሰጠው ድጋፍ የክልሎችን |

| የኦዲትጭብጦች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| | ሪፖርት በመጨመር ዕቅድና ክንውኑን በየ3ወሩ፣ በየ6ወሩ፣ በየ9 ወሩና እና በየዓመቱ ለግብርና ወይም ለንግድ ሚኒስቴር ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 31. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለክልሎች እና ለፌዴራል ሕ/ስ/ማህበራት የሕግ ጉዳዮችን በመከታተል ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| 1.3 ኤጀንሲው ቀልጣፋ የሆነ የህብረት ስራ ማህበራት ክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ | 32. ኤጀንሲውና የክልል ሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ለሕ/ስ/ማህበራት በተዘጋጁት የደንብ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት ማህበራት ስለመስራታቸውና በዚህ ዙሪያ ስላጋጠሟቸው ችግሮች በየሩብ ዓመቱ ሊከታተሉ ይገባል፡፡ |
| | 33. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ለሕ/ስ/ማህበራት ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰጧቸው ይገባል፡፡ |
| | 34. በማህበራት የሚዘጋጀው የመተዳደሪያ ደንብ በኤጀንሲው እና በሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ሊፀድቅ ይገባል፡፡ |
| | 35. የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ለተደራጁት ሕ/ስ/ማህበራት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወዘተ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 36. ኤጀንሲው በክልሎች በመገኘት የሕ/ስ/ማህበራትን እንቅስቃሴ በመገምገም ለሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ማሻሻያ ሃሳብ ሊያቀርብ እና በማሻሻያው ሃሳብ መሰረት ስለመስራታቸው ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 37. የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና የሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላት ማህበራት በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ መደበኛ የሆነ ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚያደርጉ ሊከታተሉ ይገባል፡፡ |
| 2. ኤጀንሲው በደንቡ መሠረት የተሰጠውን ሀላፊነት በብቃት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የተዘረጋ እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፡፡ | 38. ኤጀንሲው በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ የህ/ስ/ማህበራት የምርት እና ገበያ ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ መደበኛ የሆኑ የመወያያ መድረኮች (ወርክሾፖች፣ ሲሚናሮች ወዘተ) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |

| የኦዲትጭብጦች<br>(Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች<br>(Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| | |
| | 39. የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ እና በየደረጃው የሚገኙ የህ/ስ/ማህበራት ማስፋፊያ አካላት ተቀናጅተው የህ/ስ/ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት/ዋጋ/ እንዲኖራቸው እና ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 40. ኤጀንሲው ከሕ/ስ/ማስፋፊያ አካላትና ከማህበራት ጋር ፈጣን የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ (ኢሜል፣ ፋክስ፣ ፖስታና የስልክ አገልግሎት) በመጠቀም ሪፖርቶች፣ ጥናቶች፣ ህትመቶች፣ መመሪያዎችና መረጃዎችን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊለዋወጥ ይገባል፡፡ |
| | 41. በኤጀንሲውና በህ/ስ/ማስፋፊያ አካላት መረጃዎችን በተፈለገው ቦታና ጊዜ ለማግኘት እንዲያስችል በዳታ ቤዝ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ስርዐት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 42. ኤጀንሲው እና የህ/ስ/ማስፋፊያ አካላት በሕብረት ስራ ጠቀሜታ፣እንቅስቃሴና እድገት ዙሪያ ለተደራጅዎችና ለባለድርሻ አካላት በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ ሊፈጥሩ ይገባል፡፡ |
| | 43. ኤጀንሲው በድጋፍ (በሪፖርት አደራረግ፣ በስልጠና አሰጣጥና ስልጠናው ያመጣው ውጤት አለካክ ዘዴና ቁጥጥር ወዘተ) ዙሪያ ከማስፋፊያ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ (MoU) ሊኖረው ይገባል፡፡ |